የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

**ቁጥር** አ1162/11/783

**ቀን** ኅዳር 20 ቀን 2015 ዓ.ም.

**ለእነ አቶ ዘለሌ ጸጋሥላሴ (19 ሰዎች)**

**<u>አዲስ አበባ</u>፣**

**ጉዳዩ፡- <u>የቦርዱን ውሳኔ ስለማሳወቅ፤</u>**

እነ አቶ ዘለሌ ጸጋሥላሴ (ሁለት ሰዎች) በነሃሴ 02 ቀን 2014 ዓ.ም በጻፉት አቤቱታ የፓርቲው ፕሬዝደንት ከፓርቲው በአልለቀቁበት ሁኔታ በደንቡ መሰረት ያልተሟላ ስራ አስፈጻሚ ጠቅላላ ጉባኤ ለማድረግ በመጣደፍ ላይ ስለሚገኝ ደንቡ እንዲታገድ እና ፕሬዝደንቱ የት እንደተሰወሩ እንዲረጋገጥ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባኤ በ22/12/14 ዓ.ም እንዳይደረግ ስላመለከቱ፤

በነሃሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም ሰለሞን ተሰማ (ፒ.ኤች.ዲ) በጻፉት አቤቱታ የፓርቲው ፕሬዝደንት ፓርቲውን ከለቀቁ በኃላ አራት የስራ አስፈጻሚ አባላት እና ባልተሟላ የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት ከደንቡ ውጪ ምክትል ፕሬዝደንት እና ስራ አስፈጻሚ አባላትን ማጽደቃቸው ህገወጥ ነው በማለት እነዚህ አካላት የሰጧቸው ውሳኔዎች እንዲታገዱ ስለጠየቁ፤

በነሃሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም አስካለ ደምሌ ባቀረቡት አቤቱታ ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጪ የሆነ ስራአስፈጻሚ ቡድን ከፓርቲ ሃላፊነት ማሰናበት እና ስም ማጥፋት ስለፈጸሙብኝ ቡድኑ እንዲታገድ ስለጠየቁ፤

በነሃሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም እነ አቢናስ አለማየሁ (13 ሰዎች) በጻፉት አቤቱታ ከህግ ውጪ የተመሰረተ ስራአስፈጻሚ እንቅስቃሴን ቦርዱ እንዲያስቆም ስላመለከቱ፤



ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

በመስከረም 06 ቀን 2015 ዓ.ም እነ ሰናይት ታደገ (ሁለት ሰዎች) በጻፉት አቤቱታ ፓርቲው በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ያልተቀመጡ ምክትል ፕሬዝደንት፤ የጽ/ቤት ሃላፊ እና ስራ አስፈጻሚዎች እየተመራ ስለሆነ ይህ እስከሚስተካከል ድረስ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ላልተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም ብለው ስላመለከቱ፤

በጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ እነ ሰለሞን ተሰማ በተመሳሳይ የስራ አስፈጻሚው እና ምክትል ፕሬዝደንቱ እያከናወኑ ያሉት ህገወጥ ተግባራት እንዲቆም ስለጠየቁ፣

ቦርዱ ከዚህ በላይ የተገለጹት አቤት ባዮች ያቀረቡትን የተለያዩ ቅሬታዎች ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ መርምሯል። በዚህ መሰረት የሁሉም የፓርቲው አባላት አቤቱታዎች ዋና መነሻ የፓርቲው ደንብ ድንጋጌዎች ተጥሰዋል የሚል በመሆኑ፤ ይህንን አይነት አቤቱታዎች በፓርቲው አባላት ሲቀርብ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 15.2.2፤ 15.2.4፤ 24 እና ተከታዮቹ መሰረት በቅድሚያ በፓርቲው የቅሬታ አፈታት ሥነሥርዓት መሰረት ለሚመለከተው የፓርቲው የውስጥ አደረጃጀት መቅረብ ያለበት በመሆኑ፤ ቅሬታ አቅራቢዎች በቅድሚያ ይህንን ሂደት ተከትለው ቅሬታቸውን ለፓርቲው ለሚመለከተው አካል አቅርበው እልባት ማግኘት አለማግኘት ጥረት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የፓርቲን የውስጥ አለመግባባት ቦርዱ እንዲያየው ሊቀርብ አይገባም ሲል ወስኗል።

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
Deputy Chairperson National Electoral Board